# 2ቱ አይጦች



8 ተረቶች

[illegible] አረፋ አብዱልቃድር 0912-889077

Awatta
Awatta Books

Scanned by CamScanner

## ኢጋዘንና አንበሳ

በአንድ ጫካ ውስጥ የሚኖር አንድ ኢጋዘን ነበር፡፡ ይህ ኢጋዘን ሁለት ረጃጅም ቀንዶች አሉት፡፡ ረጅም እና ቀጫጭን እግሮቹን እየተመለከተ በጣም ይኩራራል፡፡

አንድ ቀን አንድ አንበሳ ሊበላው ያባርረው ጀመር፡፡ ኢጋዘኑ ፈጣን እንስሳ በመሆኑ በጣም በመሮጥ ከአንበሳው ጥቃት ራሱን አድኖ ወደ ጥቅጥቅ ወዳለ ጫካ ገባ፡፡

በጫካው ውስጥ ሲሄድ በድንገት የዛፍ ቅርንጫፍ ቀንዶቹን ያዘበት፡፡ለራሱ "ቀንዴ ችግር ሲያጋጥመኝ ከጠላቴ ጋር የምጣላበት ስለሆነ በጥንቃቄ ልይዘው ይገባል" አለ፡፡

ሞራል፡- "የሚያገለግል ዕቃ ከጌጣጌጥ በጣም ይበልጣል"





Scanned by CamScanner

## ቁራና እንስራ

በአንድ ሞቃታማ ቀን አንድ ቁራ ለረጅም ሰዓት ከበረረ በኋላ በጣም ደክሞት ውሃ ጠማው፡፡ በዛፍ ላይ ቁጭ ብሎ ውሃ በአይኑ ይፈልግ ጀመር፡፡ በድንገት ዓይኑ አንድ እንስራው ላይ አረፈ፡፡ ቁራው እንስራው አጠገብ ሄዶ ውሃውን ለመጠጣት ቢሞክርም እንስራ ውስጥ የነበረው ውሃ ትንሽ ስለነበር መድረስ አልቻለም፡፡

ቁራው ለትንሽ ጊዜ በምን ዘዴ ውሃውን መጠጣት እንደሚችል እያሰበ እያለ በዙሪያው ብዙ ትናንሽ ድንጋዮችን ተመለከተ፡፡ በድንገት አንድ ሐሳብ መጣለት፡፡ ድንጋዮቹን አንድ በአንድ ለቅሞ እያንዳንዱን ድንጋይ እንስራው ውስጥ ወረወረ፡፡ ድንጋዮቹ እንስራው ውስጥ ሲጠራቀሙ ውሃው ወደ ላይ ብቅ አለ፡፡

ቁራው የውሃ ጥሙ እስከሚረካ ድረስ ጠጣ፡፡

ሞራል፡- "በበቂ ሁኔታ ጠንክረህ የምትሞክር ከሆነ የችግርህን መልስ በፍጥነት ልታገኝ ት፡






## 2ቱ አይጦች 1

የከተማው አይጥ ማይክ እና የገጠሩ አይጥ ታይክ ጥሩ ጓደኛሞች ነበሩ፡፡ አንድ ቀን ማይክ ጓደኛውን ታይክ ለመጠየቅ መኪና ተሳፍሮ ወደ ገጠር ሔደ፡፡

ታይክ ጓደኛውን ሲያየው በጣም ተደሰተ፡፡ ለምሳ የስንዴ አገዳዎችንና ትኩስ ፍራፍሬ አቀረበለት፡፡ ማይክ ፍራፍሬዎቹንና የስንዴ አገዳዎቹን እየተመለከተ "አንተ እዚህ የጉንዳኖች ህይወት ስትኖር እኔ በከተማ ውስጥ በምቾት ተከብቢያለሁ፡፡ ከእኔ ጋር ወደ ከተማ የምትመጣ ከሆነ በቂ ጣፋጭ ምግቦች ታገኛለህ " በማለት ጓደኛው ነገረው፡፡



ታይክ በሀሳቡ ተስማምቶ ያሉትን ንብረቶች በሙሉ ጭኖ ከጓደኛው ማይክ ጋር ወደ ከተማ መጣ፡፡ ከተማ ባያቸው ነገሮች ተደንቀ፡፡ ማይክ ዳቦ፣ ኩኪሶች፣ ፍራፍሬ እና ብዙ አይብ አቅርቦለት በምግቡ ለመደሰት ተረጋግተው እንደተቀመጡ አንድ ትልቅ ድመት በመስኮት በኩል ዘሎ መጣ፡፡



ድመቱን እንደተመለከቱ፡ ሁለቱም አይጦች በሚችሉት ፍጥነት እራሳቸውን ለማዳን ወደ ጉድጓድ ሮጠው አመለጡ፡፡ ድመቱ እንደተመለሰ ሁለቱም አይጦች ከጉድጓድ ውስጥ ወጡ፡፡ ታይክ በጣም ፈርቶ "ደህና ሁን ማይክ! ምንም እንኳን ምቾት እና ከበቂ በላይ የሚጣፍጥ ጣፋጭ ምግብ ቢኖርህም እኔ ግን ተራ ምግብና ቀላሉን የገጠር ኑሮ ይሻለኛል፡፡ ምክንያቱም ለኑሮዬ ከፍራቻ ነፃ የሆነ ቦታ እመርጣለሁ" ብሎት ሄደ፡፡

ሞራል፡- የመጀመሪያው አስፈላጊ ነገር ደህንነት ነው






Scanned by CamScanner

## አንበሳ እና አጋሮቹ

አንበሳ፣ ቀበሮ፣ ተኩላና ሌሎች የዱር እንስሳት ያገኙትን ነገር እኩል ተካፍለው ሊመገቡ ተስማምተው አንድ ላይ ለአደን ሔዱ፡፡ በጋራ ሆነው አጋዘንን አድፍጠው አደኑ፡፡ ያደኑትን በስምምነታቸው መሠረት እኩል ለመካፈል ስብሰባ ተቀመጡ፡፡ አንበሳ ራሱን ለማሳየት በመንቀባረር የዱር እንስሳቱን መቁጠር ጀመረ፡፡ ከዛም እንዲህ አለ "የመጀመሪያውን ድርሻ እወስዳለሁ ምክንያቱም መብቴ ስለሆነ፡፡ እንደዚሁ የጫካ ንጉስ በመሆኔ ሁለተኛውን እወስዳለሁ፡፡ በተጨማሪ እጅግ በጣም ጠንካራ ስለሆንኩኝ ሶስተኛውንም እወስዳለው" አለ፡፡ ከዚያም በሌሎቹ ላይ ማፍጠጥ እና ማጓራት ጀመረ፡፡ ንግግሩን በመቀጠል "ከናንተ ውስጥ ማንኛውንም አይነት ጥያቄ የሚያነሳ ካለ እናንተን ጨምሬ ሁሉንም ስጋ እበላለሁኝ" አላቸው፡፡

ሞራል፡- ከኃይለኛ ጋር የሽርክና ውል ሲያደርጉ ጥንቃቄ ይፈልጋል





## ከርከሮና ቀበሮዎች

አንድ ቀን ከርከሮ ዛፍ ስር ቆሞ ጥርሶቹን በግንድ ላይ ይፈትጋል፡፡ በአከባቢው የሚዘዋወሩ ሁለት ቀበሮዎች ከርከሮው በዛፍ ግንድ ላይ ጥርሶቹን ሲሞርድ ተመለከቱት፡፡ ከርከሮውን እንደተመለከቱት ሳቁና ከሁለቱ አንዱ "ለምንድነው የሚታደንም ሆነ ሌላ ማንኛውም የሚያሰጋ ነገር በሌለበት እንደዚህ የምታደርገው?" በማለት ጠየቀው፡፡

ከርከሮ "እውነት ነው! ነገር ግን ምንጊዜም በህይወት ውስጥ አደጋ አለ፡፡ አደጋው በሚመጣ ጊዜ ጥርሴን ለመሞረድ ጊዜ አይኖረኝም፡፡ ስለዚህ የሚጠቅመኝን ንብረት ጊዜ ባለኝ ነፃ ጊዜ ውስጥ ዝግጁ ማድረግ አለብኝ" በማለት ቀበሮዎቹ ላነሱት ጥያቄ ምላሽ ሰጣቸው፡፡

ሞራል፡- የባከነን ጊዜ መመለስ አይቻልም





Scanned by CamScanner

## አውራ ዶሮ እና የከበረ ድንጋይ

ከእለታት አንድ ቀን አንድ በጣም የተራበ አውራ ዶሮ ለራሱና ለጫጩቶቹ ምግብ ለመፈለግ መሬቱን በጥፍሩ መጫር ጀመረ፡፡ ለትንሽ ጊዜ ያህል መሬቱን እንደጫረ እንደ እድል ሆኖ ውድ የሆነ የከበረ ድንጋይ አገኘ፡፡

ውድ የሆነውን የከበረ ድንጋይ አነሳና "ምናልባት ይህ በጣም ውድ የከበረ ድንጋይ ሊሆን ይችላል፡ በአሁን ሰአት ግን ለእኔ አንድ ነጠላ ጥሬ በቆሎ ከጌጦች ሁሉ የሚበልጥ ዋጋ አለው፡፡" በማለት ለራሱ ተናገረ፡፡

ሞራል፡- " ውድ የከበሩ ድንጋዮች ረሐብን ማስታገስ አይችሉም"





## ተንኮለኛ ቀበሮ እና ቀይዋ ዶሮ



በአንድ እርሻ ቦታ የምትኖር አንድ ቀይ ዶሮ ነበረች፡፡ ጊዜዋን የቤቷን ፅዳት በመጠበቅና ምግቧን በመሰብሰብ ታሳልፋለች፡፡

በእርሻ ቦታ ካለው ከዶሮዋ ቤት ብዙም ሳይርቅ ተንኮለኛ ቀበሮ ከሚስቱ ጋር ይኖር ነበር፡፡ ይህ ተንኮለኛ ቀበሮ ዶሮዋን ካየት ጊዜ ጀምሮ "ይህች ቀይ ዶሮ የግዴታ ስጋዋ በጣም ለስላሳ መሆን አለበት! እሷን በትልቁ ማሠሮዬ ውስጥ ባበስላት እወድ ነበር" በማለት ያስባል፡፡



Scanned by CamScanner



አንድ ቀን ተንኮለኛው ቀበሮ ትልቅ ቦርሳውን ይዞ ተነሳ ፡፡ ለሚስቱ "ቀይዋን ዶሮ ለእራታችን ለማድረግ ልይዛት ስለምሄድ ውሃ አፍልተሽ ጠብቂኝ" በማለት ተንኮለኛው ቀበሮ ቀይዋ ዶሮ ወደ ምትገኝበት ቦታ ሄደ፡፡

ተንኮለኛው ቀበሮ የቀይዋ ዶሮ ቤት ቢደርስም ዶራዋ ምግብ ለማብሰል የምታነደውን እንጨቶች ለቃቅማ ለማምጣት ከቤቷ ወታ ስለነበር ሳያገኛት ቀረ፡፡ወደ ቤትዋ እስከ ምትመለስ ድረስ ተንኮለኛው ቀበሮ ከቤትዋ አጠገብ ካለው ዛፍ ኋላ ተደብቆ ይጠብቃት ጀመር፡፡





ተንኮለኛው ቀበሮ ቀይዋ ዶሮ ወደ ቤትዋ ስትመጣ ከርቀት ተመለከታት፡፡ ቀድሟት ወደ ቤትዋ ገባ፡፡

ቀይዋ ዶሮ የምታነደው እንጨት ሰብስባ ወደ ቤቷ ገባች፡፡ የቤቷን በር በምትዘጋበት ጊዜ ተንኮለኛው ቀበሮ ትልቁን ቦርሳ ከፍቶ ሊይዛት ሲል አየችው፡፡



Scanned by CamScanner



ቀይዋ ዶሮ በመደንገጥ የያዘችውን እንጨት በትና ቤቱ ውስጥ በሚገኝ ትልቁ ምሰሶ ላይ በራ ወጣች፡፡

"አንተ ቀበሮ ምንም ተንኮለኛ ብትሆንም እኔን መያዝ አትችልም" አለችው፡፡

ተንኮለኛው ቀበሮ "ለምን ያህል ጊዜ ነው እዚያ ላይ ተሰቅለሽ መቆየት የምትችይው?" ሲል ጠየቃት፡፡



ቀበሮ የዶሮዋ መውረድ የማይቀር መሆኑን ቢያውቅም ዶራዋ በጣም ብልህ እና ጠንቃቃ በመሆኗ እሷን መያዙ ቀላል እንደማይሆን አውቋል፡፡

እሷን ለማስፈራራት ግን "እይዝሻለሁ" እያለ ቤቷ ውስጥ መሯሯጥ ጀመረ፡፡

ቀይዋ ዶሮ በበኩሏ የቀበሮውን በቤቷ ውስጥ መሯሯጥ ስትመለከት "በሚደክመው ጊዜ ከቤቱ ወጥቶ ይሄዳል" ስትል አሰበች፡፡





Scanned by CamScanner



ተንኮለኛው ቀበሮ በጣም በፍጥነት ዙሪያውን እየተሽከረከረ መሮጥ ጀመረ። ቀይዋ ዶሮ በምሰሶው ላይ ተቀምጣ በአይኗ ትከተለዋለች። ነገር ግን ቀበሮ ምን እየሰራ እንደነበር አልተረዳችውም።

ምስኪኗ ቀይዋ ዶሮ በአይኗ ስትከተለው ብትቆይም ከትንሽ ቆይታ በኋላ ስለዞረባት በምሰሶው ላይ ሚዛኗን ጠብቃ መቆየት ባለመቻሏ በአታላዩ ቀበሮ ትልቅ ቦርሳ ውስጥ ወደቀች።





ቀበሮ ቦርሳውን ቆልፎ በትከሻው ላይ አንጠለጠለና ወደቤቱ መሔድ ጀመረ።

ሆኖም ቀበሮው በዶሮዋ ቤት ውስጥ ባደረገው መሯሯጥ ስለደከመው ቦርሳውን ከጎኑ አስቀምጦ ለማረፍ ቁጭ እንዳለ እንቅልፍ ወሰደው።

ቀበሮ በተኛበት ቀይዋ ዶሮ በቦርሳው ውስጥ እንዳለች ነቃች። ቦርሳውን ከፍታ አንገቷን ብቅ በማድረግ ስትመለከት ቀበሮው መተኛቱን በመመልከቷ ከቦርሳው ውስጥ ቀስ ብላ በመውጣት ቦርሳውን በድንጋዮች ሞልታ በፍጥነት ወደ ቤቷ ሄደች።



Scanned by CamScanner



ተንኮለኛው ቀበሮ ከእንቅልፉ ሲነቃ ምን እንደተፈጠረ ስላላወቀ በድንጋዮች የተሞላውን ቦርሳ ተሸክሞ ወደ ቤቱ ሔደ፡፡

ቤቱ እንደደረሰ ሚስቱ "ቀይዋን ዶሮ አመጣህ?" ስትል ጠየቀችው፡፡ "አዎን! አዎን" በማለት ከመለሰ በኋላ "ውሃው ሞቋል ወይ?" ሲል ጠየቃት፡፡ ሚስቱም "አዎን ውሃ ሞቋል" ስትል መለሰችለት፡፡ ቦርሳውን አንስቶ ወደ ሞቀው ውሃ ገለበጠው፡፡ ድንጋዮቹ ወደ ሞቀው ውሃ ሲገለበጡ የሞቀው ውሃ በተንኮለኛው ቀበሮና ሚስቱ ላይ ተደፍቶ አቃጠላቸው፡፡

ከዚያን ቀን ጀምሮ ቀበሮ ተንኮል መስራት መጥፎ መሆኑን አወቀ፡፡

ከዛን ቀን ጀምሮ ቀይዋ ዶሮም በሰላምና በደስታ መኖር ጀመረች፡፡




## 2ቱ አይጦች 2



የአክስታማቾች ልጆች የሆኑ አንድ ቀጭን እና አንድ ወፍራም አይጦች ነበሩ፡፡ ወፍራሙ አይጥ በገጠር ሲኖር ቀጭኑ አይጥ በከተማ ውስጥ ይኖራል፡፡


ጊዜው ክረምት ስለነበር ቀጭኑ አይጥ የአክስቱን ልጅ ለመጠየቅ ወደ ገጠር ሄደ፡፡

ቀጭኑ አይጥ ገጠር እንደደረሰ ወፍራሙ አይጥ በጣም በመደሰት "ተወዳጅ ዘመዴ አንተን እየጠበኩኝ ነበር፣ እንኳን በሰላም መጣህ" በማለት በደስታ ተቀበለው ፡፡




በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ወፍራሙ አይጥ ቀደም ብሎ በመነሳት ጣፋጭ ፍራፍሬዎችን ለቀጭኑ አይጥ ሰበሰበለት፡፡ ቀጭኑ አይጥ በድሎት እና በደስታ በከተማ ውስጥ የሚኖረውን ኑሮ እያሰበ ወፍራሙ የገጠር አይጥ እንዴት አድካሚ ስራ እንደሚሰራ እያየ ተደነቀ፡፡






የአክስታማቾቹ ልጆች ከቁርስ በኋላ ረጅም ጉዞ በእግራቸው ይሔዳሉ፡፡ በመንገድ ላይ እየተጓዙ የከተማው አይጥ ለገጠሩ "እንዴት እንደዚህ ዓይነት ደካማ ኑሮ እየኖርክ መቀመጥ እንደምትችል ሊገባኝ አልቻለም?" እያለ ይጠይቀዋል፡፡ በድንገት 'ቋ-ቋ-ቋ' የሚል የጉጉት ድምፅ ሰሙ፡፡ "ያ የምን ድምፅ ነው?" በማለት ቀጭኑ የከተማ አይጥ ጠየቀው፡፡



ወፍራሙ አይጥ ጉጉቱ ዝቅ ብሎ በመውረድ አንስቱ ሊበላቸው መፈለጉን በማወቁ "ተጠንቀቅ" ብሎ በመጮኸ ቀጭኑን አይጥ በጉጉት ከመበላት አዳነው፡፡ "ተመስገን ፈጣሪዬ ድነናል" በማለት ፈጣሪውን አመሰገነ፡፡ ቀጭኑ የከተማ አይጥ ጉጉት በማየቱ ፈራ፡፡ በዚህም ምክንያት ወደ ከተማ መመለስ አለብኝ በማለቱ ሁለቱ ዘመዳሞች አይጦች ተያይዘው ወደ ከተማ መጡ፡፡






ከተማ እንደገቡ ወፍራሙ አይጥ በመንገድ ላይ በሚታዩት ደማቅ መብራቶችና ረጃጅም ሕንፃዎች መደነቅ ጀመረ፡፡ ብዙ ጫጫታ ሰምቶ ስለማያውቅ በመኪናዎች የጥሩንባ ድምጽ ፍርሃት አደረበት፡፡




Scanned by CamScanner



በአንድ ምሽት ሁለቱ አይጦች እየተጫወቱ እያለ ወፍራሙ አይጥ ከቤቱ ጥግ ላይ ትንሽ ዳቦ በአይጥ መያዣ ወጥመድ ላይ ተቀምጦ ተመለከተ፡፡ በገጠር ውስጥ ወጥመድ አይቶ ስለማያውቅ ዳቦውን ለመብላት ወደ ዳቦ ሲሄድ ቀጭኑ አይጥ ጭራውን በመሳብ "ቆያ! ያንን እንዳትነካ! ያ ነገር ወጥመድ ነው" በማለት አስረዳው፡፡ ወፍራሙ አይጥ ስለወጥመድ ተረድቶ ፊቱን አዙሮ እንደሄደ ሌላ ሰምቶት የማያውቀው 'ሚያው' የሚል አዲስ አይነት ድምፅ ሰማ፡፡ቀጭኑ አይጥ "ሩጥ ድመቱ ሊበላህ ተጠግቶሀል" በማለት ሲነግረው ሁለቱም አይጦች በፍጥነት ትንሽ ቀዳዳ ውስጥ ገብተው ተደበቁ፡፡





ወፍራሙ አይጥ ባጋጠሙት ነገሮች ፈራ፡፡ ከተማ ውስጥ ብዙ ጊዜ መቆየት እንደማይችል ተረዳ፡፡ ለራሱ እያንሾካሾከ " እዚህ መምጣት አልነበረብኝም" እያለ ተኛ፡፡ ሆኖም ውስጡ ፍርሀት ስለገባ እንቅልፍ ሊወስደው አልቻለም፡፡በሀሳቡ "በዚህ ትልቅ ከተማ ውስጥ ከምኖር ወደ ገጠር ቤቴ ተመልሼ መሔድ ይሻለኛል፡፡ ቀላል የገጠር ኑሮ ከዚህ ከሚያብረቀርቀው የከተማ ኑሮ የበለጠ የተሻለ ነው፡፡ ቢያንስ ገጠር ውስጥ በሰላም ምግቤን መብላት እችላለሁ" በማለት አሰበ፡፡



Scanned by CamScanner



በማግስቱ ጠዋት ቀጭኑ የከተማው አይጥ ወፍራሙን የገጠር አይጥ ጠርቶት “ስማ ዘመዴ እኔ የከተማ አይጥ ስለሆንኩኝ የገጠሩን ኑሮ ለመልመድ ከበደኝ፤ አንተም የገጠር አይጥ ስለሆንክ የከተማውን ኑሮ በቀላሉ ለመልመድ ተቸግረሀል። ሁልጊዜ አዲስ ነገር ለመልመድ የተወሰነ ጊዜ መቸገር የማይቀር ነው። ዋናው ቁምነገር በርተቶ መማርና ለማወቅ መጣሩ ላይ ነው” ብሎት በሳጥን የተሞላ ስጦታ ሰቶት ወደ ገጠር ሸኘው። ወፍራሙም አይጥ ለተሰጠው ስጦታ አመስግኖት ሄደ።



Scanned by CamScanner